# አፈር እናልብሰው

እሳት አምቦ ሲነድ ፣ በጎንደርም ይግፋ
ጎንደር ሲቀጣጠል ፣ የጎጃሙ አይጥፋ
ጎጃሜው ሲነሳ ፣ ወልዲያም ይስፋፋ
ባስፈካጊው ፍጥነት ፣ አድርጎ ቀልጣፋ
እንደ ሰደድ እሳት ፣ ጭራሽ የማይጠፋ
ለናት አገራችን ፣ የሚሆናት ተስፋ
በምድር አንቀጥቅጥ ፣ የትግል አንጋፋ
ትንፋሽ እንዳይገዛ ፣ በመባከን ይልፋ
ወያኔን አራውጡት ፣ ከምድረገፅ ይጥፋ ።

ቦግ እልም እንዳይል ፣ በተናጠል ትግል
የኔ ያንተ ሳንል ፣ ሳናደርገው የግል
ህብረትን ሳንሸሽ ፣ ፈርተን እንደ ፈንግል
ተመቻችተንለት ፣ እንዳሻው ሳይገድል
አሸናፊ ሆነን ፣ እንድንበቃ ለድል
ሁሉም በያለበት ፣ አንድ ሰው ሳይጎድል
ባንድነት ተነስተን ፣ እናስመዝግብ ገድል ።

የሻገተው ስርዓት ፣ በስብሶ መንቀዙ
በፉኖው በቄሮው ፣ አርሶ አደር ገበዙ
ስርዓቱ ተናግቶ ፣ መናጥ መወዝወዙ
እንኳንስ ሊገሉ ፣ እንኳንስ ሊገዙ
ማንቁርቱን ተይዞ ፣ ስለወጣ መርዙ
ፋታ እንዳያገኙ ፣ ጊዜን እንዳይገዙ
ውሾቹና ሃጎስ ፣ ለእስር ሳይጓዙ
መዘናጋት የለም ፣ ሁሉም ሳይያዙ ።

የባንዳ ጥርቅም ፣ ባገር ላይ የለማ
በልቶ አማይጠረቃ ፣ ከደሃ እየቀማ
በደም የሰከረ ፣ ደምን የተጠማ
የሻገተ ስርዓት ፣ በስብሶ የገማ
ገንፍሎ የወጣው ፣ ቁጭት የታመቀ
ሳር ቅጠሉ ጠልቶት ፣ በህዝብ የተናቀ
አልባሌ እርካሽ ፣ ሆኖ እንደወደቀ
ውሾም ተገንዝቦት ፣ ዘመኑ እንዳለቀ
ዛሬ ነገ እያለ ፣ እየተሳቀቀ
መቃብር ላይ ቆሞ ፣ ሞት እየጠበቀ
ውለታ እንዋልለት ፣ አለቀ ደቀቀ
አፈር እናልብሰው ፣ ቁርጡ ከታወቀ ።

ታዛቢው
February 2, 2018